# ህወሓት "ትኩሳት ነው" - ነቀርሶቹ ሌሎች

ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

የተጀመረው ተስፋ ሰጪው ተቃውሞ በያለበት እየተስፋፋ ሲሄድ ቀደም ሲል ፳፮ን የቅርቡንም " ቅንጅትን!" ያስታውሱኛል። የኹለቱንም መጨረሻዎች ሳስብ ግን ይዘገንነኛል! ለመጀመሪያው መፍትሄ " ለውጥ በሰላም ለሰላም!" በሚል ርዕስ አዲስ ዘመን ላይ ያወጣሁት ነበር። በቅንጭቡ፦

ሀ - ፩- በዚያን ጊዜ የነበረው መንግሥት ( የ.ጠ. ሚኒስትሩ) በጊዜያዊነት እንዲታወቅ፣ በስድስት ወር እንዲገደብ፣ ግዳጁም ፍጹም ሥልጣንን ከንጉሠ ነገሥቱ ለሕዝቡ በምክር ቤት አማካይነት መመለስ እንዲኾን ሲብራራም፦ ምክር- ቤቱ ላገር የሚጠቅም ዕቅድ አለኝ ከሚሉት ከአምስት የማይበልጡትን አወዳድሮ ከ ኹለት ሦስተኛ ድምጽ ያላነሰ ያገኘውን በመምረጥ ፦ተመራጩ የሥራ ባልደረቦቹን ይዞ በን. ነገሥቱ ማጸደቅ

፪- ይህ መንግሥት በሽግግር መንግሥትነት ታውቆ ይሻሻል የተባለውን ሕገ መንግሥት ያለ ምንም ጥድፊያና ጫና የለው ሕገ መንግሥት አንድ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ ሲሻሻል የኹለት ጊዜ የምክር ቤቶችን ስብሰባ በሚያዝዘው መሠረትና መንፈስ የተሻሻለውን ማስጸደቅ፤ በዚሁም መሠረት ሕዝቡ አስተዳዳሪውን መምረጥ ነበር ሳይኾን የቀረበትን ማንሳቱ ላኹን አይጠቅምም፡፤ ይህ ካልኾነ ግን "አገራችን የወገን ማለቂያ፦ የጠላትመሳለቂያ የወዳጅ መሰቀቂያ ትኾናለች።" ነበር ያልኹት"

ለ - የደርግ ግዛት ማክተሙ ያገሩን ጉዳይ በጥሞና ለሚከታተል ግልጽ ሲኾን በየካቲት ወር "NEWS NIGHT! በሚባል ዕውቁ የቢቢሲ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ወጥቼ አሜሪካን ፈርዲናንድ ማርቆስን ከፊሊፒንስ በማውጣቱ ፊሊፒንስ ክሕወት መጥፋትና ከንብረት ውድመት ድናለች። አኹንም ከፅጥታው ጉባኤ ጋር ኾና መንግሥቱን ብታወጣና ሽንጎ ጊዜያዊ መንግሥት ቢመርት ኢትዮጵያን በተመሳሳይ ዓይነት ትድናለች በማለት ተማጽኜ ነበር። ውጤቱን በፍዳ እየኖርነው ነው እያለቅነውም።

ሐ - እነዚህን ጠላቶች በስመ - ሽምግልና ሊያስገቡ ኹለቱን ወገኖች ለንደን May 27/ 91 ቀጥረው May 23 ምሽቱ ላይ ደርግን ለ፲፯ ዓመታት በቢቢሲ ፎከስ ኦን አፍሪካ በምጠዘጥዝበት ጊዜ (ከርዝራዦቹ አንዱ አኹንም እኔን በተለያየ ዘዴና መልክ የሚጠዘጥዘኝ አለ) የተዋወቅሁት መካከለኛ ሥልጣን እርከን ላይ የነበረ ወዳጄ ደውሎ፦ How much confidence do you have on the American brokerage of peace? አለኝ።፡እኔም Not very much, but why do you ask? ስለው ከተል አርጎ Why not? አለኝ እኔም ፦ Let's take these in turns, ስለው Oh! You! አለና የስደት አገሬ መንግሥትና የአሜሪካኖቹ ወኪሎች ለሦስት ቀናት ዋሽንገትን ዘግተው የሥልጣን ክፍፍልን በጎሳ ማድረጋቸውንና ምን ያህሉንም በምናውቀው ዓይነት እንደኾነ አረዳኝ። በዚያን ሰሞን ላደርግ የሞከርሁትን ማንሳቱ ቦታው ስላልኾነ ልለፈው።

ወደቀውጢው ኹኔታ ስንመለስ እንዳለፉቱ ተስፋ ሰጪዎቹ ኹኔታዎች እንዳይዳፈን፦ ጠለቅ ያለ ሃሳብን ይጠይቃል።

መ - HORN OF AFRICA ብለው ከሱዳን ከኤርትራ ጂቡቲና ሶማሌ ጋር አደባልቀው "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም ለዘላለሙ እንዲጠፋ ያቀዱት እንዴት ተጨናገፈ? በነሱ መልካም ፈቃድ! ከመሰላችሁ ይኹና !!

ርዕሴን "ሕ.ወ.ሃ.ት. ትኩሳት ነው!" ያልሁት ከላይ የጠቀስኋቸው መንግሥታት በዋናነት ሌሎቹም በኢትዮጵያ መጥፋት ተጠቃሚዎች "ቅምጥነታቸውን በማመን ነው።

ታዲያ ነቀርሳውን / ነቀርሳዎቹን ባንነቅላቸው እንኳን ማድከሙን ማሰቡና መከወኑ ቅድሚያ ሊሰጠው አይገባም።

**ፕሮፌሰሮች ጌታቸውና ሚንጋ "ቪዥን ኢትዮጵያ" ላይ መፍትሄ ሲፈልጉ በጉጉታቸው የተነሳ የተሳታፊዎቹን የትምህርት ደረጃ በማየት አንዱ እምባውን ሲያብስ ሌላው በጥልቅ መደመም ወስጥ ሲጠልቅ ያሳዝኑ ነበር። እስቲ አኹን እንኳን ዳር ዳሩን ካመሄድ መፍትሄው ላይ እናተኩር።**

**አንድዬ እናታችንና ልጆችዋን ከተከታታይ ጥፋት ያድን**

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
August 6, 2016